**Seattle**
Office of Sustainability
& Environment

# ለሲያትል የተፈጥሮ አካባቢ ፍትህ የድጋፍ ገንዘብ ያመልክቱ

የሲያትል የዘላቂነት እና የአካባቢ ጥበቃ ጽሕፈት ቤት (OSE) የአካባቢ ፍትህ የድጋፍ ገንዘብ **አሁን ማመልከቻዎችን እየተቀበለ** መሆኑን ሲያሳዉቅ በደስታ ነዉ። በዚህ አመት፣ በተፈጥሮ አካባቢ እና በአየር ንብረት ጉዳዮች ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን ማህበረሰቦች የሚመሩ እና የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ $250,000 ዶላር ይገኛል። ይህ ጥቁር፣ ተወላጆች፣ ነጭ ያልሆኑ ሰዎች፣ አዲስ ሰፋሪዎች፣ ስደተኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች፣ ወጣቶች እና ሽማግሌዎች ያጠቃልላል።

***አጠቃላይ የድጋፍ ገንዘብ ተሰጥቶ እስኪያልቅ ድረስ ወይም ፣ 20 ቀን 2024 ከምሽቱ 5 ከሰዓት (የፓሲፊክ ጊዜ) ድረስ ከሁለቱ በቀደመ*** በቅደም ተከተል የሚሆን ማመልከቻዎች ተቀባይነት እና ክለሳ ያገኛሉ። ብቁ የሆኑ አመልካቾች ለ$10,000 ዶላር ወይም ለ$25,000 ዶላር ስጦታ ማመልከት ይችላሉ።

ይህ የገንዘብ ድጋፍ ለጎሳዎች እና ለጎሳዊ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እና ከማህበረሰባቸው ጋር የአየር ንብረት ፍትህን እና የተፈጥሮ አካባቢ ወደፊት ለማራመድ የሚሰሩ የማህበረሰብ ቡድኖች ነው። ብቁ የሆነ ድርጅት ወይም የማህበረሰብ ቡድን በአሁኑ እና በቀደመው የበጀት አመት *በአማካይ $500,000 ዶላር ወይም ከዚያ ያነሰ ባጀት* ሊኖረው ይገባል። ፕሮጄክቶቹ በኪነ ጥበብ እና ትርክት ማቅረብ፣ በማህበረሰብ ትምህርት፣ በድርጅታዊ እና ማህበረሰብ አቅም ግንባታ፣ በአየር ንብረት ለውጥ መላመድ ጋር እና የመቋቋም ችሎታ፣ ክህሎት ግንባታ እና ከአረንጓዴ ስራዎች* ስልጠናዎች ጋር የተዛመዱ እና ከማህበረሰብ እቅድ ማድረግ እና ራዕይ መተለም ላይ ሊያተኩሩ የሚችሉ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተወሰኑ ናቸው።

*ስለዚህ የድጋፍ ገንዘብ የበለጠ ለመማር፣ የፕሮጀክት ሃሳብ ለመወያየት፣ ወይም ለውሳኔ የሚቀርብ አንድ ሃሳብ ለማስገባት ፍላጎት ካልዎት፣ እባክዎትን የሚከተሉትን እርምጃዎችን ይውሰዱ:*

- ከቴክኒካል እርዳታ ሰጭ አማካሪ ጋር ለመገናኘት **equityenviro@seattle.gov** ኢሜይል ያድርጉ። *ይህ ለሁሉም ፍላጎት ላላቸው አመልካቾች በብርቱ የሚበረታታ ነው።*

- ከሁለት አንዱን ምናባዊ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች ተገኝተው ይከታተሉ።
    - *ማክሰኞ፣ ነሐሴ 27ኛ ከቀኑ 12 - 1 ከሰዓት ኋላ* እዚህ በዙም አገናኝ
    - *ሰኞ፣ መስከረም 9ኛ ከምሽቱ 6 - 7 ሰዓት* እዚህ በዙም አገናኝ

እንዲሁም ደግሞ በኢሜይል ጥያቄዎችን ለመመለስ እንገኛለን እና ፍላጎት ያላቸው አመልካቾች በ equityenviro@seattle.gov ወደ እኛ እንዲደርሱ አጥብቀን እናበረታታለን። እንዲሁም ለበለጠ ለማወቅ፣ ለማመልከት እና ያለውን የድጋፍ ገንዘብ ሁኔታ ለማጣራት **seattle.gov/environment/ejfund** መጎብኘት ይችላሉ።

* ለEJ የድጋፍ ገንዘብ አላማ፣ አረንጓዴ ስራዎች ለአየር ንብረት ለውጥ እና ዘላቂነት ምላሽ በመስጠት አዉድ ዉስጥ ያሉ ያሉ ስራዎች እና ሙያዎች ተብሎ ይገለፃሉ።